# ከቅሌቶች በጭልፋ

አሰፋ ጫቦ
Dallas Texas USA

Amazon ላይ ይህንን አዲሱን ቬፐር የሚሉትን ሲጋራ ማጨሻ “$4.99 ለመላኪያ የሚሆን ክፍልና ውስድ” የሚል አነበብኩን እንደተባለው አዘዝኩ።ለማዘዝ ሁሌ እንደሚደርገው የክርዲትካርድ(Credit Card) ቁጥር ሰጠሁ። ከሁለት ቀን በኋላ “ለመላኪያ $2.99 እንደገና እንጨምራለን” አሉ። ገርሞኝ ለሁለት ብር አልሟገትም ብዬ አለፍኩት።

ትላንትና ከባንኬ email አገኘሁ። “አንድ Ecigs የሚባል ከሒሳብህ ላይ$99.99 ቆርጧልና ታውቀዋለህ ወይ?” የሚል። “አውቀዋለሁ ግን የህንን ገንዘብ ውስድ አላልኩትም” ስል “እኛም ጠርጥረን ክፍያውን አግደናል!” አሉ።
ያ ሳያነስ ዛሬ ገና በቅጡ ሳይነጋ ስልክ ተደውሎ “ከFraud Investigation Department ነን” አለችኝ። Fraud ትርጉሙ አጭበርባሪ ን፤አውናባጅና ሌላም ሌላም ማለት ይሆን?” ምነው?” ስላት ”ሰሞኑን የተገበያየኸውን እስቲ አብረን እንደናይ ነው” ብላ የአንድ ሳምንቱን ግብየቴን ቆጠረችልኝና “ይህ ሁሉ ያንተ ነው ወይ?” ስትለኝ ፤ የEcigs ልክ አለመሆኑን ነግሬ “እኛም አውቀናል ጎድጓድ ምሰናል!”አይነት ብላ ገንዘቤ እንዳልተነካ ነገረችኝ ከተጀመረ አይቅር ብዬ ዛሬ ባንኩ ሔጄ ያንን $2,99ኙንም አሰረዝኩ። “አንዴ ቁጥርህን ስለሚያቁ ሊጠቀሙበት ይችላሉና አዲስ ካርድ ይሻላሐል!’ ብላኝ ነባሩን በመቀስ ቆራርጣ ጣለችው። በቋፍ እንድንሔድ እያደርርጉን እኮ ነው!!

******

ሌላው ቅለቴ የዚህ የጋምቢያ ፕሬዝዳንት ጉዳይ ነው።አሁንማ “የነበረው!” ሆኗል። ቢሊዮን አመት እነግሳለሁ ብሎም ነበር አሉ። ብቻ ቢሊዮኑ ሲመነዘር ወደ 20 ምናምን አመት ሆነ። ምርጫ ተደርገና “መሸነፌን ተቀብያለሁ!” አለ።በማግስቱ “አልተቀበልኩምና እንደገና ይቆጠርልኝ!” አለ። በዚያ ማግስት ይሁን እንጂያ ፓርላማ የሚለውን ጠርና “ነገሩ እስኪታጣራ 3 ወር ተጨማሪ ጊዜ ስጥተነዋል!” አለ ፣ፓርላማው።

ነገሩ እንዲህ ሲጠነዛ የምእራብ አፍርቃ ትብብር የሚባለው “ወይ ወርድ ወይ ወዮልህ!” አለና ወታደር ላከበት።”እወርዳለሁ ግን ቀን ስጡኝ” ብሎ ሶስት ቀን ተሰጥቶት አሁን ተሳፍሮ አገር ለቆ ወጣ። ሥራውን ያውቃልን የጁን እንዳይገኝ መሆኑ ነው።ሶስቱን ተጨማሪ ቀን የፈለገው ወርቅ ፤ዶላርና ሌላም ያከማቸውን ከየተደበቀበት አውጥቶ ለመጫን ነበር።
“አፍሪቃዊ መሆኔ ያሳፍረኛል!”ለማለት ትንሽ ዳድቶኝ ነበር። ከዚያ ኢትዮጵያዊ መሆኔ፤አፍሪቃዊ መሆኔ፤ ኢትዮጵያም ዲሞክራሲያው ረፑብሊክ መሆንዋ ትዝ አለኝ። “የኛው ጉድ!” ማለት ይሻላል ብዬ መሆን አለበት። “ምነው የዚህ እንደምእራብ አፍርቃው በምስራቃ አፍሪቃም ባለጠመንጃ ትብብር ቢኖር?” አሰኘኝ።

*****

ሌላው የዶናልድ ትራምፕ ቅለቴ ነበር። ሰውዬው ቅሌታም መሆኑን አንድም ቀን ከዶና አስተባብሎ አያውቅም። ባይሆን በላይ በላዩ ይጨምርበታል እንጅ። የትራምፕ ቃል አቀባይ በመጀመሪያ በሰጠው ጋዜጣታው መግለጫ “የትራምፕን መመረቅ ለማየት የወጣው ሕዝብ ብዛት እስከዛሬ ተሰምቶም ታይቶም አያውቅም” አለ። ጋዜጦችና መገናኛ ዜደዎች ሁሉ የሕዝቡን ብዛት ከኦቦማ ጋር በማነጣጠተር በምስል የተደገፍ አውጥተውት የነበረውን አውገዘ። ውሸት ነው አለ።
በነጋታው የትራምፕ አዲስ ሹም የሆነች ሴት አንድ ጋዜጠኛ ተለቪዥን ላይ አፈጠጣት። “ይህንን በማስረጃ የተደገፈ እውነት እንዴት ትክዳላችህ?” ሲላት “እናንነት የምታዩት እውነትና እኛ የምናየው እውነት ይለያያል!” አለች። ሲተረጎም “እውነት የሚባል ነገር የለምና እንደተርጓሚው ነው!” ማለትዋ ነው መሰለኝ።

ሌላው በምስል የተደገፈ ቅሌቴ የትራፕምና የሚስቱ ሥልጣን ሊረከቡ ሲመጡ፤አቦማና ሚሼል ደረጃ ላይ ሆነው ሲጠብቋቸው የሆነው ነው። ትራምፕ ከመኪና ይወርድና ሚስቱን ዞር ብሎ እንኳን ሳያያት ደርጃውን ይወጣታል። ቆይታ ተከትላው ትወጣለች።ያኔም አልተቀበላትም። ከዚያ ለሚሼል ያመጣችውን ስጦታ ስተሰጥ አቦማ ይረዳታል።ሰውየው የሚዘረጠጥው ሴት በጠቅላላው ብቻ ሳይሆን የገዛ ሚስቱንም የሚየከብር አይመስልም።
ከዚያ ትራምፕና ባለቤቱ ግብዣ ላይ ሲደንሱ የሚያሳይ ፊልም አየሁ። ተዋደው ተጋብተው ሳይሆን ፖሊስ አዘገድዷቸው የመጡ የሚመስል ነገር አለው።
ከቅሌትና አወናብጅ ይሠውረን!